# <u>ዘመቻ መረሳ</u>

(ክፍል አንድ)

በአህመድ አባቡልጉ

የተከበራችሁ አንባብያን ይህቺን ጽሑፍ ለመጻፍ ያኔሳሳኝ ላለፉት ሁለት አስርት ዓምታት ከነበሩኝ ገጠመኞችና ተመክሮዎች አንጻር ዛሬም በኢትዮጲያ እየተፈጸመ ያለው ሁኔታ፥ በከስተቶች መዴጋገምና ብልሹነት የተነሳ የማውቃቸውን ዕውነታዎች ላላዩትና ላልሰሙት ማካፈሉ ለግንዛበም ሆነ ለአንዳንድ ጥንቃቄዎች ይረዳል ብዬ በማሰብ ነው፡፡

በሀገሪቱ በተካሄዱት የለዉጥ ሂደቶች በአወንታ ሊጠቀሱ የሚገባቸዉ ተግባራት እንደመኖራቸዉ በዓሉታም የሚነሱት በርካቶች ናቸዉ፡፡ በተለይም በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የተፈፀሙ ጥፋቶች ሰፊና የጎሉ ናቸዉ፡፡ ያለፈዉም ስህተት ለዛሬዉ ከስተት ትምህርት መሆን እያቃተዉ ይልቁንም በመንግስትና በገዢዉ ፓርቲ ዘንድ እንደ መልካም ተመክሮ መወሰዳቸዉ በዝምታ ሊታለፍ አይገባዉም ከምል እምነት ነዉ፡፡

የኢህአዴግ መንግስት ከህዝብ ጀርባ በርካታ በደሎችን ስፈጽም እንደኖረ ብዙ ተብሎለታል፡፡ ያልተነገረው ከተነገረው እጅግ እንደምብስ ደግሞ ጥርጥር የለውም፡፡ በህዝቦች ላይ የሚፈፀመው በደል እስካልተገታና ፍትህ እስካልተረጋገጠ ድረስ ፈርጀ ብዙ ትግል አይቀሬ ነው፡፡ ለፍትህ መረጋገጥ በሚደረገው ፍልሚያ የትናንቱን ነባራዊ ሁኔታ ማወቅ ለዛረው ጉዞ በእጅጉ ይጠቅማል፡፡ በተለይ ትናንትን ያላዬ ወጣት የዛረን ብቻ ይዞ እንዳይጓዝ ያለፈውን ከስተት ከፋም ለማ ማሳወቅ ግዴታ እንደሆነ እረዳለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ህዝቡም ዕውነታን የማወቅ መብት አለውና፡፡

ይህን ዕዉነታ ለመግለፅ ሲነሳ በማንም ግለሴሰብ ወይም ወገን ላይ በተለዬ ሁኔታ የማነጣጠር ዓላማ ከቶም የለኝም፡፡ ዓላማዬ የነበረዉን ዕዉነታ መረዳት በቻልኩትና ማስረዳት በሚችለዉ መጠን ብቻ ማቅረብ ነዉ፡፡

የኢህአዴግ ሰራዊት ሃገር ተቆጣጥሮ ስልጣን ከጨበጠ ሃያ አንድ ዓመታት ቢያልፉም በነዚህ ሁሉ ጊዚያት ሰራዊቱም ሆነ መሪውቹ መጠነ ሰፊ በደል ከመፈጸም እንዳልወጡ እስከ ዛረ ያለው እውነታ መልካም መገለጫ ነው፡፡አምባገነንነት ጣራ ነክቶ፥ ፍትህና ነጻነት ደብዛው ጠፍቶ፥ ፍርሃት በደልና ጉስቅልና በቦታው ነግሶ ሃገር የጥቂቶች ሁና መታየቱ ኢህአዴግ ምን ይዞ መጥቶ ምን ይዞ ሊሄድ ነው ያስብላል፡፡

ስልጣን እንደተቆጣጠረ ለአድ ወር በጫካው ህግ ሃገር የገዛው ይህ አካል የሽግግር ወቅት ቻርተር አዘጋጅቶ ለአራት ዓመታት ቢያዘግምበትም ብሎም ላለፉት አስራ ሰባት ዓመታት የሚመጻደቅበትንና ለጥቂቶች ብቻ ፍትሃዊ የሆነዉን ህገ-መንግስት አጽድቆ በሱ ሽፋን ያሻውን ሲፈጽም ብኖርም ተግባሩ ሁሉ ከመጀመርያው ህግ የወጣ አይደለም ፡፡

ለህገ-መንግስቱ ማስፈጸሚያ የሚወጡት ህጎች ሁሉ በህዝቦች መብት ላይ የሚረማመዱ፥ አለ የተባለውን የመብት ቀዳዳ ሁሉ ለመድፈን የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ የዜጎች መሰረታዊ ሰባአዊ መብቶች ከቶም የማይከበሩበት፥ የሃገር ሃብትና ንብረት ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ፍጡሮችም የኢህአዴግ የሆኑ እስከመስል እንዳሻው ማሰር፣ መግረፍና መግደልን መብቱ በማድረግ ከወረሳቸው ከፉ ስርዓቶች ባልተለዬ ሁኔታ ግፉ ተባብሶ ይገኛል፡፡

ይህ ኢህአዴግ በሕዝብ ላይ የሚፈፀመው የጭካኔ ተግባር የሚመነጨው በድርጅቱ ዉስጥ ካለው የሕዝብ ፍርሃት፥ ጭንቀትና እምነት ማጣት ነው፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ

ከወደቀ ዳግም እንደማይነሳ ካለው ስጋት በመነሳት ላለመውደቅ ስል የእውር ድምብሩን ከፊቱ ያገኘውን ሁሉ እዬረጋገጠ ማለፉን ባህሉ አድርጎታል፡፡ ሳይነካ ተነካሁ፥ ሳይገፋ ተገፋሁ እያሌ ከሌላው ብቻ ሳይሆን ከራሱም ጭምር እየተጣላ እዚህ ደርሰዋል፡፡ ከለጋ እድመው ጋር ሲነጻጸር ትዕግስት አልባነትና ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ጎልቶ ዪታይበታል፡፡

ድርጅቱ ከራሱ በላይ ለሃገር የማይጨነቅ መሆኑን በግልጽ እያሳዬ ሲሆን ከመሪዎቹ አንደበት የሚወጡትም ቃላት ኢህአዴጎችና ድርጅታቸው ከሌሉ ሌላው ምን ልጠቅም የምሉ ይመስላል፡፡ ለምሳሌ ከጥቂት ወራት በፊት ዋና ፀሃፊው ሟቹ አቶ መለስ ፓርላማቸው ላይ ቀርበው እንደተናገሩት «አልቃዕዳ ኢትዮጵያ ገባ» ማለታቸው ኢህአድግ ኖረም አልኖረ እሳት ጭሮ ለማለፍ ይመስላል፡፡ በህዝብ መሃል ጥርጣሬና ስጋት መፍጠርም የዘወትር አላማቸው ነውና፡፡

ለዚህ ጽሁፍ ወዳነሳሳኝ ወቅታዊ ጉዳይ ልመለስ፡፡ ርዕሱን ያነበበ ሁሉ በአእምሮው ጥያቄ ማጫሩ አይቀርም፡፡ ይህን ስም ሳነሳ ከምንም ተነስቼ አይደለም፡፡ ከዚህ ስም ጀርባ ብዙዎቻችን የማናውቀው ነገር ግን ብዙዎቻችንን የሚመለከቱ ክስተቶች ስለነበሩና ዛሬም በገሃድ እዬታዩ ካሉት መሰረተ ሰፊ የመብት ጥሰቶች ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ነው፡፡

ኢህአዴግ ከቶም ከማይቀበላቸው መሰረታዊ የሰበዓዊ መብቶች መካከል  ላለፉት ሃያ ዓመታት በፅናት ከታገላቸው አንዱ በነፃነት የመደራጀት መብትን መንፈግ ነው፡፡ ነፃ ማህበራት የድሞክራሲ ስርዓት መሰረቶች እንደሆኑ ቢታመንም፥ ለድሞክራሲያዊ ስርዓት ፈር ቀዳጅ ነኝ የሚለው ኢህአዴግ ግን የነፃ ማህበራት ጠንቅ ሆኖ ኖሯል፡፡

ምንም እንኳን አንዳንድ ማህበራት የራሳቸው የሆነ መሰረታዊ ችግሮች ቢኖርባቸውና በህግ አግባብ መታረም ቢገባቸውም ኢህአዴግ ግን በመረጠውና በተከተለው የጅምላ ፍረጃ «ነፃ ማህበራት የአብዮታዊው ድሞክራሲ ጠንቆች ናቸው» በሚል ስሌት የመብት ገፈፋውን ባህሉ አድርጎት ኖረዋል፡፡

ለዚህም ተግባሩ ግብታዊ የሆነ ትንኮሳና ጣልቃገብነት ስልት ሳይሆን የሚከተለው በረጂሙ አቅዶ፥ ዓላማውን የሚያሳኩለት በዚህ ተግባር የተካኑ ሰዎችን መድቦ፥ በጀቱን አስልቶ እንደ አንድ የልማት ተግባር ብዙ ደክሞበታል፡፡ በዚህም ሁኔታ የሰራተኛና የሙያ ማህበራት የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል፡፡ ድርጅቱም በዚህ መሰሪ የከፍፍለህ ግዛ ዓላማው በመካን ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ ዛሬም ይህንኑ እየደጋገመ ይገኛል፡፡

ኢህአዴግ ለዚህ የመከፋፈልና የማጥቃት ዓላማው መሳካት ድርጅቶችን ብቻ ሳይሆን ግለሰቦችንም የጥቃቱ ዕላማ በማድረግ ቀላል የማይባሉ በደሎችን ፈፅመዋል፡፡ ድርጅቱን በመቃረን የተሰለፉትን ብቻ ሳይሆን ከፓርቲው ገለልተኛ ሆነው በትግሉ ሂደት ግን አጋር የነበሩ ግለሰቦችን ጭምር ከዕምነት ማጣትና ፍፁም ጠባብ ከሆነ አመለካከት በመነሳት የጥቃት ዕላማ አድርጓቸዋል፡፡

ኢህአዴግና መንግስቱ በስልጣን ዘመናቸው የሰራተኛ፣ የመምህራንና የጋዘጠኞች ማህበራትን እንድሁም የዕምነት ተቋማትን በግልፅም በስውርም አጥቅተዋል፡፡ ህገ-መንግስት ባልነበረባቸውም ሆነ ባሌባቸው ዓመታት ለፈፀሟቸው በርካታ ኢ-ሰብዓዊና ኢ-ፍትሃዊ ተግባራት የድርጅቱን መዋቅሮችና በየደረጃው የሚገኙ መንግስታዊ ተቋማትን በህገ-ወጥ ከመጠቀሙም በላይ የፍትህ ስርዓቱን በማዛባት ጭምር በደል ፈፅመዋል፡፡

ይህ ተግባር ከህዝብ ያልተሰወረ ቢሆንም እንደዬሁኔታው ለጉዳዩ ቀረበታ ያላቸው ሰዎች አንድም ቀርበው ከማየትና ከመስማት አልፆም በአንዳንድ ክስተቶች ከነበራቸው ተሳትፎ አንፃር ህያው ምስክሮች ናቸው፡፡ እኔም ከነዚህ ሰዎች አንዱ ነኝ፡፡

ለኢህአዴግ አድናቆት ኖሮኝ ባያውቅም በመጀመርያዎቹ ዓመታት የነበረው ሃገራዊ የለውጥ እንቅስቃሴ የህዝቡን የፍትህና የእኩልነት ጥያቄዎች በከፊሉም ይመልሳል በሂደትም የሚሰፋ ጅማሮ ነው የሚል ዕምነት ነበረኝ፡፡ ከነበርኩበትም የመምህርነት ሙያ ዙሪያ በተለይ በመምህራን ማህበር አመራር ዘንድ ጎልተው ይታዩ የነበሩ የህዝቦችን እኩልነትና መብት በቅንነት ያለመቀበል ችግሮች ጎልተው የታዩበት ወቅት ሲለነበር የህዝቡን መሰርታዊ ሰበዓዊ መብቶች ለመጠበቅ በነበረው ትግል እንደ አንድ አጋር ይሆናል ከሚል ዕምነት የድርጅቱም ሆነ የመንግስቱ አካል ካልሆነው ነገር ግን በግልፅ እንደሚታወቀው የቅርብ ቁርኝት ከነበረው የመምህራን ማህበር ውስጥ ሚና ነበረኝ፡፡

በወቅቱ ከማህበሩ ጀርባ የመነጩ ግልጽም ድብቅም ተልዕኮዎች በሰፊዉ ተከስተዋል፡፡ በተለይ በማህበሩ የበላይ አመራሮች በሰፊዉ ይራመዱ የነበሩት አቋሞች በመምህራን መካከል መከፋፈልን በመፍጠር ለወራት የዘለቀ የሃሳብ ፍጭትን ቀስቅሶ ነበር፡፡ ችግሮቹ ለመምህራን በማህበራቸዉ ዙሪያ የተከሰተ በመሆኑ የሌላ አካል ጣልቃገብነት ሳያስፈልግ በራሳቸዉ የዉስጥ ትግል ተፈጥሮአዊ በሆኔ ሂደት ዕልባት አግኝተዉ ቢሆን በተሻሌም ነበር፡፡

ለስብዕናቸዉ ቀናኢ በመሆን ከማህበሩ ጀርባ የነበሩትን ድብቅ ተልዕኮዎች ለማክሸፍ የታገሉት መምህራን ተቃዉሞአቸዉና ትግላቸዉ መቸዉንም ቢሆን የማይታበል ሀቅ ሲሆን እንደ ጉልህ ስህተት ሊጠቀስ የሚችለዉ ግን በኢህአዴግ ላይ ዕምነት መጣላቸዉና የትግል አጋር ማድረጋቸዉ ነዉ፡፡ መንግስትም እንደ ህግ አስከባሪነቱ የዜጎችን መብት የሚጥሱ፤ የዜጎችን ስብዕና የሚያስተናንሱ ግሌሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ሲያጋጥሙ በህግ አግባብ ማሬምና ፈር ማስያዝ እንጂ የዜጎችን በነፃነት የመደራጀት መብት መተላለፉ ለድብቅ ዓላማዉ ማሳኪያ እንጂ ከዘላቂ የድሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አንፃር ጉልህ ስህተት ነበር፡፡ ይልቁንም_የተፈጠረዉን አጋጣሚ «ዉሻ በቀዴደዉ… »እንድሉት በለመደዉ ስልቱ ገብቶበት ተጠቅሞበታል፡፡

ከኢመማ ጀርባ የነበሩት ችግሮች ምንጫቸዉ አንድ ብቻ ባይሆንም ለጊዘው በማህበሩ ጉዳይ የኢህአዴግ መንግስት የተከተለውን አቅጣጫና የፈፀማቸው ተግባራት ላይ ማተኮር እሻለሁ፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ ከዚህ ተግባሩ ባለመታረሙ ነውና ዛሬም መጠነ ሰፊና የሚሊዮኖችን ህሊውና ጥያቄ ውስጥ ያስገባ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እዬፈፀመ ያለው፡፡

ኢህአዴግ በህዝባዊ ድርጅቶች ጉዳይ የሚከተለው ዋንኛ ዓላማው ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ አባላቱን በዕምነት በአመለካከት ወዘተ በመከፋፈል አንድነትን ማጥፋት ነው፡፡ በዚህም ስልት ድርጅቶቹን ወይም ማህበራቱን ማዳከም ከቻለም መቆጣጠር ነው፡፡ በተጓዳኝ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ስራዎችን በመስራት ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚነሱበትን ጥያቄዎች፣ ክሶችና ወቀሳዎችን የማዳፈን ስራ መስራት ነው፡፡ በዚህም ሂደት ተጨማሪ ህገ-ወጥ ተግባራትን በመስራት ኢ-ፍትሃዊነቱን ይበልጥ ያሰፋበት ወቅት ነው ያሳለፈው፡፡

በአጭሩ በተለይ በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር /ኢመማ/ ዙሪያ የተከሰተው ዕውኔታ ጸረ ህገ-መንግስትና መሰረተ ሰፊ የመብት ጥሰት መገለጫ በመሆኑና በይፋ የሚታወቁትም ሆኑ የማይታወቁት ወጥተው ብነገሩ ለህዝቡ ግንዛበና ጥንቃቄ

ስለሚጠቅሙ እንድሁም ከጉዳዩ ጀርባ የነበሩት ግለሰቦች ዓመታትም ፈጅተዉ ያልታረሙ መሆናቸዉን ሳይ ድርጊታቸዉን ለህዝብ ማሳዬቱ አስፈላጊ ሆኖ ስላየሁ ነዉ።

ኢህአዴግ በኢመማ ጉዳይ ቀጥተኛ የጣልቃገብነት ስራውን የጀመረው በ 1985/ኢ. ዘ. አ./አጋማሽ ላይ ነበር፡፡ ወቅቱም ከፍተኛ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የለውጥ ጥማት ያዬለበት ጊዜ ነው የነበረው፡፡ በአዲሱ የፖለቲካ አቅጣጫ የብሔር ብሔረሰቦች የመብት ጥያቄ የጎላበት፥ አመለካከቶች በሰፊው የሚጋጩበት፥ የውይይት ባህል ባልዳበረበት ማህበረሰብ ልዩነቶች በቀላሉ ወደ ግጭት የሚያመሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ፖለቲካዊ የመቻቻልና የመተሳሰብ ባህላችን ባለመዳብሩ ቡድንተኝነት በቀላሉ እንድፈጠር ዓይነተኛ ምክንያት የሆነበት ወቅት ነው የነበረው፡፡

ይህ ያለመቻቻል፣ ያለመተሳሰብና የቡድንተኝነት ስሜት ከወቅቱ የፖለቲካ ቅኝት ጋር ተዳምሮ ወደ ኢመማም ጎራ በመግባቱ በአካባቢው የተፈጠረውን ሁከት ምክንያት በማድረግ ኢህአድዴ ይጠቅመኛል ብሎ ያሰበውን የመከፋፈልና የማጥቃት ዘመቻውን ከፈተ፡፡ እነሆ ሁለት አስርት ዓመት ደፈነ፡፡ በዚህ የጣልቃገብነትና የመብት ጥሰት ተግባር ዋነኞቹን ተዋናዮች/መዋቅሮች/እና የነበራቸውን ሚና ከዚህ ቀጥለን በአጭሩ እንመልከት፡፡

## የፓርቲው /የኢህአዴግ/ሚና

ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ በኢመማ ጉዳይ የጣልቃገብነት ተግባር ፈጽሟል፡፡ በየደረጃው በተለያዩ አካላት የተፈፀሙትን መሴል ተግባሮችንም በበላይነት መርቷል፡፡ በማዕከል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳዎች የፓርቲውን መዋቅሮች በቀጥታ በማህበሩ የውስጥ ጉዳይ እንድገቡ በመፍቀድ የመሰረታዊ ሰብዓዊ መብት የሆነውን በነፃነት የመደራጀት መብት ነፍጓል፡፡

በወቅቱ /1985/ ሃገሪቱ ህገ-መንግስት ያልነበራት ቢሆንም በስራ ላይ የነበረው የሽግግር ወቅት ቻርተር የዜጎችን በነፃነት የመደራጀት መብት ያለገደብ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑ የፓርቲው ተግባር ህገ-ወጥ ነበር፡፡ ፓርቲዉ ከፈፀማቸዉ ተግባራት ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል፦

በጥር ወር 1985 በፓርቲው መዋቅር በወረደው መመሪያ መሰረት መምህራንን ግልፅነት በጎደለውና በከፊልም አስገዳጅ በሆነ መልኩ በየትምህርት በቶቻቸው ሳይሆን በግልፅ በማይተዋወቁበት በወረዳ ማዕከላት በማሰባሰብ በየወረዳው የፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ሃላፊዎች በሚመሩት ስብሰባዎች እንድገኙ ከተደረገ በኋላ በወቅቱ ኢመማን በጊዜያዊነት ይመሩ የነበሩት የበላይ አካልት እዬፈፀሟቸው ናቸው የተባሉ በከፊልም በመምህራን ዘንድ የሚታወቁ ላለመግባባት መንስዔ ሲሆኑ የነበሩትን ነጥቦች እንደ መነሻነት በማቅረብ በዚህም የመምህራንን ስሜት በመከፋፈል አማራጭ የአደረጃጀት አቅጣጫን መከተል ወቅቱ የሚጠይቀው ግዴታ መሆኑን በማሳሰብ ምርጫ አልያም ውክልና ለማለት በሚያዳግት መልኩ አዲስ የአስተባባሪ ኮሚተ ማደራጀት ጀመሩ፡፡

ሂደቱም ሆን ተብሎ በጥድፍያ የተከናወነ ሲሆን ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዘ ውስጥ የዞንና የክልል ዕርከኖችን በማለፍ በሃገር አቀፍ ደረጃ አዲስ አስተባባሪ ኮሚተ ተቋቋመ፡፡ ምርጫዉም ከወረዳ እስኬ ሀገር ዓቀፍ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በፓርቲው አመራሮች ወይም ካድረዎች የተመራ ሲሆን አስፈላጊ የሆነውንም ወጪ ሁሉ የሸፈነው ድርጅቱ ነበር፡፡

በሂደቱም የተሳተፉት መምህራን የፓርቲው አባላት የነበሩ፥ ገለልተኛ አቋም የነበራቸውና እንድሁም ፓርቲውን አምርሬው የሚጠሉና ተቃዋሚ አመለካከት

የነበራቸው ሲሆኑ በዚህ ጉዳይ እንድሰባሰቡና በሂደቱም እንድሳተፉ ያደረጋቸው ከፍ ብሎ ለመጥቀስ የሞከርኩት ምክንያት /የለዉጥ አቀንቃኝነትና የማህበሩ ጊዜያዊ አመራር ይከተል የነበረዉ አቋም ልዩነት/ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ የመደራጀት ነፃነት ተከብሯል ብሎ ስዋሽ የኖረው ኢህአድግ በዚህ መልኩ የጀመረውን ህገወጥ ተግባር አጠናክሮ በመቀጠል አዲስ የተመረጠውን አስተባአሪ ኮሚቴና ቀጥሎም በቋሚነት በቦታው የተተካውን አካል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ፍፁም በሆነ የበላይነት ሲቆጣጠርና ነጻነት ስነፍገዉ ኖሯል፡፡ ምንም እንኳን ከመሰረታዊ ማህበራት ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ በተዘረጋው መዋቅር ውስጥ የነበሩት አመራሮች ብዙዎች የድርጅቱ አባላት ወይም ደጋፊዎች ሳይሆኑ የተፈጠረው የለውጥ ሂደት በተለይም የትምህርት ፖሊሲው ደጋፊዎች ብቻ የነበሩ ቢሆንም አጠቃላይ የማህበሩ እንቅስቃሴ ከፓርቲውና ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ሆኖ አያውቅም፡፡

ስለ ፓርቲው ጣልቃገብነት ባነሳሁት ነጥብ ላይ አንድ ጉልህ የሆነ ማስረጃ ልጥቀስ፡፡ በየካቲት 1985 የተቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ  የማደራጀት ስራ ሲሰራ ቆይቶ በሰኔ ወር በቋሚ ተተካ፡፡ በአመራሩም ውስጥ ከትግራይ፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ህዝቦችና ከሃረሪ ክልሎች እንድሁም ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ መስተዳድሮች ተወካዮች የነበሩ ሲሆን በማህበሩ ፕሬዚዳንትነት የተመረጡትም ከአማራ ክልል የተወከሉት ነበሩ፡፡

አመራሩ በፓርቲውና በመንግስት አስፈፃሚ አካላት ስር ሆኖ ሲታገዝ ቢቆይም ከተለያዩ አቅጣጫ ከሚደርስበት ተፅዕኖ የተነሳ አንድነቱን ጠብቆ መቀጠል ተሳነው፡፡ በዚህም ወቅት ኢህአዴግ በነካካው እጁ ገብቶበት የፓርቲው ከፍተኛ ባለስልጣናት/ በማህበሩ ጉዳይ ውክልና የወሰዱ/ከአንድ ወር በላይ በወሰደና  ከዘጠና ሰዓታት በላይ በፈጀ ኢህአድጋዊ ግምገማ አጠቃላይ ኮሚቴው ከሃላፊነት እንድወገድ ወስነዉ አመራሩን በተኑ፡፡

ይህን ግምገማ መርተው ውሳኔውንም ያሳለፉት በኢህአዴግ ተወክለው በህዝባዊ ማህበራት ጉዳይ ላይ በተለይም በኢመማ የድርጅታቸው ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን ስሰሩ የኖሩት የዚህ ፅሑፍ ርዕስ አድርጌ የጠቀስኳቸው አቶ መረሳ ረዳ ናቸው፡፡ ግምገማውንም ያካሄዱት በዚህ ተግባር ላይ ረዳታቸው ከነብሩትና በወቅቱ የአዲስ አበባ ኢህአድግ ጽ/ቤት ኃላፊ ከነበሩት/በህወሃት ክፍፍል ወቅት ከድርጅቱ የተባረሩ ናቸው/አቶ ተስፉ ማርያም ከተባሉ ከፍተኛ የድርጅት አመራር ጋር ነበር፡፡

እኔም እነኝህ ሁሌት የፓርቲው ከፍተኛ ባለስልጣናት ከማህበሩ ጀርባ ወሳኞች የነበሩ መሆናቸውን ያወኩት በዚህ የግምገማ ወቅት ይደርሰኝ ከነበሬ አንዳንድ መረጃና የግምገማውንም ውጤት በሰማሁበት ጊዜ ነበር፡፡

ከረዳታቸውም መወገድ በኋላ በብቸኝነት በዚሁ ተግባራቸው የቀጠሉት አቶ መሬሳ የድርጅቱን መዋቅር ብቻ ሳይሆን የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን/የሚኒስቴር መ/ ቤቶችንም ሆኔ የክልል መስተዳድሮችን/በቀጥታና በተዘዋዋሪ በማህበሩ ጉዳይ ባሻቸው በማዘዝ ያም ሳይበቃ በፍትህ ጉዳይ ጭምር ጣልቃ ስገቡ ቆይተዋል፡፡

እኚህ ግሌሰብ ከመጋረጃ ጀርባ ሲፈፅሙ የኖሩት ተግባር በኢህአድግ ሚዛን ውለታ ሆኖ ያካበቱትም ተቋማትን የማጥቃት ልምድ ክብር ተሰጥቶት በአሁኑ ጊዜ መንግስት ባቋቋመው የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የሃይማኖት ጉዳዮች ድሬከቶሬት ጄኔራል ተብሌው መሾማቸው ድርጅቱ ያንን መጥፎ ተመክሮውን በተጠናከሬ መልኩ ሊቀጥልበት እንደፈለገና በተለይ በሃይማኖት ጉዳዮች ከፋፍሎ ለማጥቃት፥ ልዩነቶችን በማስፋት የርስ

በርስ መጠቃቃትን ለመቀስቀስ እንዳቀዴ አመልካች ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ ቢሮ በማህበራት የዉስጥ ጉዳይ የሚፈፀሙ የጣልቃ ገብነት ተግባራትን የሚያቅድ፣ የሚያስፈፅምና የሚቆጣጠር ከመሆኑም ባሻገር በተቃዉሞም ሆኔ በደጋፊነት የተሰለፉትን ግለሰቦች ይከታተላል፣ ይሰልላል ወዘተ፡፡

በማህበራት ጉዳይ የፓርቲውን መዋቅር፣ የአስፈፃሚውንና የፍትህ ዘርፉን በማቀናጀት ሲመሩ የኖሩት አቶ መረሳ አሁን ባለው የሃጌሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም በአማኞችና በእምነት ተቋማት ላይ እዬደረሴ ላለው የጥቃት ዕርምጃ መሪ ተዋናይ እንደሚሆኑ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

ምንም እንኳን በህዝብ ላይ እዬደረሴ ላሌው በደል የበላዮቻቸው /ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርና ሚኒስትር ዴታዉ/ከሃላፊነታቸው ጋር የሚመጥን ተጠያቂነት ቢኖርባቸውም፥ እንድሁም በህዝብ ዘንድ ዕለታዊ ዕይታና ግንኙነት ቢኖራቸውም ከጀርባቸው ያለውን ድብቅና በልምድ የተካኔ ሃይል ህዝቡ ልገነዘበው ይገባል፡፡ የዘመቻዉ መሪም ይህ አካል መሆኑ ግልጽ ነዉ። በየደረጃዉ የነበሩት የፓርቲዉ መዋቅሮች ከዚህ ክፍል በሚተላለፍላቸዉ ድርጅታዊ መመሪያ መሰረት በማህበሩም ሆነ በሁለቱም ወገን በነብሩት አመራሮች ላይ በግልጽም በድብቅም ጥቃት ሲፈጽሙ ኖረዋል። ከማህበሩም ሆነ ከአካባቢዉ እስከተለየሁበት እስከ 1994 ድረስ ይህ ተግባር ያለማቋረጥ ሲፈጸም ኖሯል።

በዚህ የኢህአድግ ክንፍ አመራር የመንግስት አስፈፃሚ አካላትና የፍትህ ዘርፎች የፈፀሚቸውን ተግባራት በቀጣይ ክፍሎች ለማየት እንሞክራለን።

*Contact:- ababulgua@gmail.com*